የገንዘብ ሚኒስቴር

MINISTRY OF FINANCE

መመሪያ ቁጥር 1063/2017

የታክስ ኦዲት የሚከናወንበትን ሥርዓት እና የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚወጣበትን አኳኋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

DIRECTIVE NUMBER 1063/2025

TAX AUDITS CONDUCTING PROCEDURES AND ISSUING TAX ASSESSMENTS DIRECTIVE NUMBER 1063/2025

2017 ዓ.ም

2025

የታክስ ኦዲት የሚከናወንበትን ሥርዓት እና የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚወጣበትን አኳኋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1063/2017

የታክስ አስተዳደር ውጤታማ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ለማድረግ ግልጽ እና ውጤታማነትን የሚያረጋግጥ የታክስ ኦዲት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የታክስ ኦዲት የሚከናወንበት ሥርዓት ውጤታማ፤ ቀልጣፋ እና ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ የታክሱ ባለስልጣን ባለሙያዎች እና ታክስ ከፋዮች ያለባቸውን ኃላፊነት የሚደነግግ እና የሚመሩበት ግልጽ እና አፈጻጸሙን የሚያሳይ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 136(2) ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የታክስ ኦዲት የሚከናወንበትን ሥርዓት እና የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚወጣበትን አኳኋን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1063/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤ በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) **"የታክስ ኦዲት"** ማለት በእነዚህ ሳይወሰን ታክስ ከፋዩ ያቀረባቸውን የታክስ ስሌቶች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እና ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ የሚፈለገውን ትክክለኛውን የግብር እዳ ለመወሰን የታክስ ከፋዩ የሂሳብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የታክስ ስሌቶች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ስልታዊ በሆነ ዘዴ በታክስ ባለስልጣኑ

TAX AUDITS CONDUCTING PROCEDURES AND ISSUING TAX ASSESSMENTS DIRECTIVE NUMBER 1063/2025

WHEREAS, it is deemed necessary to establish clear and efficient tax audit procedures to enhance the effectiveness and accountability of the tax administration system;

WHEREAS, it is necessary to provide clear and practical guidance and responsibilities to the Tax Authority officials and taxpayers for the effective, efficient, and transparent implementation of the tax audit process;

NOW, THEREFORE, in the exercise of the powers vested in the Ministry of Finance under Article 136(2) of the Federal Tax administration Proclamation No.983/2016 the following Directive is issued.

SECTION ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Directive may be cited as a "Directive on Procedures for Conducting Tax Audit conducting procedure and Issuing Tax Assessments directive number 1063/2025".

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Directive:

1) **"Tax audit"** means a systematic examination of a taxpayer's books of account, records, documents, tax declarations and other relevant information by the Tax Authority, conducted for the purpose of determining the accuracy of the taxpayer's tax filings and assessing the correct amount of tax liability owed, including any interest, penalties, and fines.

የሚመረመሩበት እና አግባብነት ባላቸው የታክስ አዋጆች እና ደንቦች መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ከሶስተኛ ወገን የሚገኙ መረጃዎችን ጨምሮ የታክስ ስሌቶች፣ ደጋፊ ሰነዶች እና ሌሎች መረጃዎች የሚመረመሩበት ሥርዓት ሲሆን፣ አጠቃላይ ኦዲት፣ በጭብጥ ላይ የተመሰረተ ኦዲት፣ የዴስክ ኦዲት፣ የተመላሽ ኦዲት፣ የማሸጋገሪያ ዋጋ ኦዲትን እና የማጭበርበር ምርመራን ይጨምራል።

2) **"አጠቃላይ ኦዲት"** ማለት ታክስ ከፋዩ በሁሉም አግባብነት ባላቸው የታክስ አዋጆች መሰረት ግዴታውን የተወጣ እና ሁሉንም የታክስ አይነቶች የመክፈል ግዴታውን በተሟላ እና በትክክለኛ መንገድ የተወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ የታክስ ከፋዩን የፋይናንስ ሰነዶች፣ የታክስ ስሌቶች፣ የሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መዛግብት ሁሉንም የታክስ አይነቶች በሚመለከት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ በዝርዝር እና በጥልቀት የሚመረመርበት ሥርዓት ነው።

3) **"በጭብጥ ላይ የተመሰረተ ኦዲት"** ማለት በታክስ ከፋዩ የሂሳብ ሰነዶች ላይ አጠቃላይ ኦዲት ማድረግ አስፈላጊ በማይሆንበት ጊዜ በታክስ ባለስልጣኑ በተመረጡ ገቢን በመደበቅ፣ ተገቢ ያልሆነ ተቀናሽ በማግኘት ወይም በተለየ የታክስ አዋጅ እና ደንብ መሰረት ግዴታን ባለመወጣት እና በመሳሰሉት በተጠረጠረ ታክስ ከፋይ ላይ ወይም በሌሎች ምክንያቶች በጭብጥ ላይ የተመሰረተ ምርመራ የሚደረግበት ነው።

4) **"የዴስክ ኦዲት"** ማለት ወደ ታክስ ከፋዩ የስራ ቦታ በአካል በመሄድ ምርመራ ማድረግ ወይም የንግድ ስራውን እንቅስቃሴ በሚመለከት ዝርዝር ምርመራ ማድረግ ሳያስፈልግ ታክስ ከፋዩን በሚመለከት ያሉትን ሰነዶች፣ መዛግብት እና የታክስ ስሌቶች መመርመር ሲሆን፣ ምርመራው የሚካሄደው የቀረቡትን ሰነዶች እና መረጃዎች በማየት ወይም ተጨማሪ ማብራሪያ ወይም የሰነድ ማስረጃ ጭምር በመጠየቅ ሊሆን ይችላል።

5) **"የተመላሽ ኦዲት"** ማለት ከተገቢው በላይ የተከፈለ ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን ጥያቄ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በታክስ ባለስልጣኑ የሚከናወን ኦዲት ነው።

6) **"የማጭበርበር ምርመራ"** ማለት ከታክስ ስወራ ጋር የተያያዘ የማጭበርበር ተግባር መፈጸሙን

A tax audit may include, but not limited to, a review of tax returns, supporting documents, and other/ information including from 3rd parties to ensure compliance with the applicable tax proclamations and regulations and includes comprehensive audit, issue-oriented audit, desk audit, refund audit, transfer pricing audit and fraud investigation

2) **"Comprehensive audit"** means a thorough and extensive examination of a taxpayer's financial records, tax returns, accounting books, and other relevant documents for multiple taxes and specific periods, aimed at determining the full and accurate tax liability of the taxpayer across all tax types and compliance with all applicable tax proclamations.

3) **"Issue-oriented audit"** means an audit that focuses on specific issues or concerns identified by the Tax Authority, such as suspected underreporting of income, improper deductions, or non-compliance with a specific tax proclamation or regulation or any other reasons, without necessarily conducting a full audit of all financial records.

4) **"Desk audit"** means an audit that is conducted based on a review of taxpayer's available documentation, records, and tax returns, without physical inspection of the taxpayer's premises or a detailed examination of the underlying business operations. A desk audit is typically carried out by reviewing submitted documents or data and may involve requests for further clarifications or documents.

5) **"Refund audit"** means an audit conducted by the Tax Authority to verify the correctness of a taxpayer's request for a refund of overpaid taxes

6) **"Fraud investigation"** means an inquiry or investigation initiated by the Tax Authority to detect, investigate, and prevent fraudulent activities related to tax

ለማረጋገጥ፤ ለመመርመር እና ለመከላከል በታክስ ባለስልጣኑ ተነሳሽነት ታክስ ስወራን፤ ሆን ተብሎ በቀረበ የተጭበረበረ መረጃ ወይም ታክስን የመሰወር ወይም የመቀነስ አላማን መሰረት በማድረግ የተፈጸመን ሌላ የማታለል ተግባር በተመለከተ የሚከናወን የማጣራት ወይም የምርመራ ተግባር ነው።

7) ***"የማሸጋገሪያ ዋጋ ኦዲት"*** *ማለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተከናወኑ ግብይቶች ዋጋ በገንዘብ ሚኒስቴር በወጣው የማሸጋገሪያ ዋጋ መመሪያ እና በአለም አቀፍ ደረጃዎች መሰረት የገበያ ዋጋ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በታክስ ባለስልጣኑ የሚከናወን ኦዲት ነው።*

8) **"አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ"** *ማለት ታክስ ከፋዩ የታክስ ህጎችን የጣሰ በመሆኑ ምክንያት አግባብነት ባለው ህግ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት መሆኑን በመግለጽ የታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ የሚሰጠው ማስታወቂያ ነው።*

9) ***"የማስፈጸሚያ ትዕዛዝ"*** *ማለት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ እና የአስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያን ጨምሮ ያልተከፈለን ታክስ፤ በዘገየበት የሚከፈልን ወለድ፤ አስተዳደራዊ ቅጣትን እና የማስፈጸሚያ ወጪዎችን ለማስከፈል በህግ ሰነድነት እንዲያገለግሉ በታክሱ ባለስልጣን በጽሁፍ የሚሰጡ ማስታወቂያዎችን ይጨምራል።*

10) **"ቅድመ-የተሻሻለ ስሌት"** *ማለት የታክስ ባለስልጣኑ ቀደም ሲል በቀረቡ የታክስ ስሌቶች ወይም የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች ላይ ማስተካከያ ለማድረግ ማቀዱን በመግለጽ ለታክስ ከፋዩ የሚሰጠው የማሻሻያው ስሌት ረቂቅ ነው። ይህ ማሻሻያ የታክስ ባልስልጣኑ ባደረገው ግኝቶች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ይህም በመደበኛ ክለሳዎች፣ ኦዲቶች ወይም ሌሎች የህግ ተገዢነት ፍተሻዎች ወቅት የተለዩ ልዩነቶችን ሊያካትት ይችላል። የቅድመ የተሻሻለው ስሌት የመጀመሪያው ግምገማ ሊለወጥ እንደሚችል ለግብር ከፋዩ በይፋ የሚገልጽ ማስታወቂያ ሆኖ ያገለግላል፤ በዚህም ግብር ከፋዩ የመጨረሻው ስሌት ከመውጣቱ በፊት ለቀረቡት ለውጦች ምላሽ ለመስጠት ወይም ለመቃወም እድል ይሰጠዋል። ይህ ማስታወቂያ የታክስ ተገዢነትን የማረጋገጥ ሂደት አካል ሲሆን በታክስ አዋጁ ውስጥ በተቀመጡት የህግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚሰጥ ሲሆን፣ ግብር ከፋዩ ማንኛውንም ተቃውሞ ወይም ማብራሪያ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያቀርብ ግልጽ መመሪያዎችን ይዟል።"*

evasion, deliberate misrepresentation of facts, or other forms of deceptive conduct aimed at evading or reducing tax obligations.

7) **"Transfer pricing audit**" means an audit conducted by the Tax Authority to assess the pricing of transactions between related parties or affiliated entities, ensuring that such transactions are conducted at arm's length as defined by applicable transfer pricing directives issued by the Ministry of Finance and international standards.

8) **"Notification of administrative penality"** means a formal written communication issued by the Tax Authority to taxpayers, informing them of the imposition of an administrative fine pursuant to the provisions of the relevant tax proclamation for a violation of the tax proclamations.

9) **"Enforcement orders"** means a formal notification issued by the Tax Authority, including the notice of tax assessment and the written notification of administrative fines, which serve as legal documents for the recovery of outstanding taxes, penalties, fees, interest on late payment, administrative fines, and enforcement costs.

10) **"Preliminary amended assessment**" means an initial assessment issued by the Tax Authority to a taxpayer, proposing adjustments to the taxpayer's previously filed tax returns or assessments. This amendment is based on the findings of the Tax Administration, which may involve discrepancies identified during routine reviews, audits, or other compliance checks. The preliminary amended assessment serves as a formal notice to the taxpayer that the initial assessment is subject to change, providing the taxpayer an opportunity to respond or contest the proposed changes before the final assessment is issued. This notice is part of the process of ensuring tax compliance and is issued in accordance with the legal provisions set forth in the tax proclamation, with clear instructions for the taxpayer to submit any objections or clarifications within a specified time frame.

11) **"የታክስ ኦዲት ሥርዓት"** ማለት ታክስ ከፋዩ በታክስ ህጎች መሰረት ግዴታውን እየተወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ በታክስ ባለስልጣኑ የሚከናወን መደበኛ የምርመራ ሥርዓት እና ዘዴ ሲሆን፤ በኦዲት ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውለውን የተቃርኖ እና የተቃርኖ ያልሆነ ሥርዓት የሚያጠቃልል ነው።

12) **"አዋጅ"** ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው።

13) በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ እና ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት እና ሃረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

14)**የመመሪያው አላማዎች**

የዚህ መመሪያ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

1) የታክስ ኦዲትን እና የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማውጣትን የሚመለከቱ የፌዴራል መንግስት አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊ የሚሆኑበት የተሟላ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፤

2) የታክስ ኦዲት አሰራር እና የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚወጣበት አኳኋን ወጥነት ያለው፤ ግልጽነት የሰፈነበት፤ በመላ ሂደቱ የታክስ ከፋዩ መብት የሚጠበቅበት መሆኑን ማረጋገጥ፤

15) **የተፈጻሚነት ወሰን**

1) ይህ መመሪያ የተመላሽ ኦዲት፤ የዴስክ ኦዲት፤ በጭብጥ ላይ የተመሰረተ ኦዲት፤ አጠቃላይ ኦዲት እና የማጭበርበር ምርመራን ጨምሮ የታክሱ ባለስልጣን በሚያከናውነው ማናቸውም የታክስ ኦዲት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) ይህ መመሪያ የታክስ ስሌት ማስታወቂያን ጨምሮ የታክስ ኦዲት የሚደረግ መሆኑን ስለማስታወቅ ግዴታ፤ ስለኦዲት ዝግጅት፤ አሰራር እና የማጠናቀቅ ሂደት እንዲሁም ለእያንዳንዱ የኦዲት ደረጃ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ ይወስናል።

ክፍል ሁለት

11) **"Tax audit procedures"** means the formal processes and methodologies employed by the Tax Authority in conducting tax audits to determine a taxpayer's compliance with applicable tax proclamations which procedures encompass both contradictory and non-contradictory procedures, each designed to address different circumstances in the audit process.

12) "**Proclamation**" means the Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016.

13) Words and phrases used in this Directive but not defined herein shall have the respective meanings ascribed to them under the Proclamation.

3. Objectives

The objectives of these directives are:

1) to provide a comprehensive framework for the implementation of the provisions of Federal Proclamation concerning tax audits and the issuing of tax assessment.

2) to standardise the process of tax audits, promote transparency, and ensure that the rights of taxpayers are respected throughout the tax audit and assessment process.

4. Scope of Application

1) These directives apply to all forms of tax audits, including refund audits, desk and field audits, issue-based audits, and comprehensive audits as well fraud investigation conducted by the Tax Authority.

2) The Directives outline the requirements for notification, preparation, execution, and completion of audits,including the issuing of assessments and the time limits for each stage of the audit and assessment process.

SECTION TWO

የቅድመ ኦዲት ሥራዎች

PRE-AUDIT ACTIVITIES

16)የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚላክባቸው ሁኔታዎች

በአዋጁ አንቀጽ 27 እና 28 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የሚላከው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፦

1) በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ባቀረበው የታክስ ማስታወቂያ መሰረት ሊከፈል የሚገባው ታክስ በተሟላ ሁኔታ ያልተከፈለ ከሆነ፤
2) በታክስ ባለስልጣኑ የተከናወነው ኦዲት ተጨማሪ ያልተከፈል ታክስ መኖሩን ያረጋገጠ ከሆነ፤
3) ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 26 እና 27 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ፤
4) የታክሱ ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩ ታክስ በማጭበርበር ድርጊት ላይ ለመሰማራት ያሰበ መሆኑን የሚጠቁሙ ጉልህ መረጃዎች አሉ ብሎ ሲያምን::

5. Conditions for Issuance of Tax Assessment Notice

Without contravening the provisions of Articles 27 and 28 of the Proclamation, the issuance of a notice of tax assessment shall be established under the following conditions:

1) When the tax declared within the prescribed time frame has not been paid in full.
2) When an audit by the Tax Authority reveals that additional tax is due.
3) When the conditions of Articles 26 and 27 of the Proclamation are met.
4) When in the judgement bof the Tax Authority, there are serious indications that the taxpayer intends to evade taxes.

17) ለኦዲት የሚደረግ ዝግጅት እና ዕቅድ

1/ ለታክስ ከፋዩ የኦዲት ማስታወቂያ ከመላኩ በፊት የታክሱ ባለስልጣን የኦዲቱን ስራ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ አለበት:: ይህም ዝግጅት የታክስ ከፋዩን የሂሳብ ሰነዶች በሚገባ መመርመርን፤ ብቃት ያለው የኦዲት ቡድን መሰየምን፤ እና የተሟላ የኦዲት ዕቅድ ማውጣትን ይጨምራል::

2/ የኦዲት እቅድ ለኦዲቱ ምክንያት የሆኑትን ከታክስ ከፋዩ ጋር የተገናኙ ስጋቶችን መለየት፤ የኦዲት ስራ የሚከናወንበትን ዘዴ መምረጥ፤ የሚመረመሩትን ሰነዶች አይነት መወሰን እና ቃለመጠይቅ ወይም ምርመራ የሚደረግባቸውን ሰዎች መለየትን ያካትታል::

6. Audit Preparation and Planning

1) Before the issuance of the audit notice, the Tax Authority shall initiate the necessary preparations for the audit. This shall include a thorough review of the taxpayer's records, the selection of a qualified audit team, and the formulation of a comprehensive audit plan

.

2) The audit plan shall identify the specific risks associated with the taxpayer that has necessitated the audit, outline the audit approach, specify the documentation to be examined, and identify any interviews or examinations to be conducted.

18)የታክስ ኦዲት የሚደረግ መሆኑን ስለማስታወቅ

1) የታክሱ ባለስልጣን በታክስ ከፋዩ የስራ ቦታ የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ከሚጀመርበት ከአስር (10) ቀን በፊት ይህንኑ ለታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት:: በስጋት ላይ

7. Notification of Tax Audit

1) The Tax Authority shall notify the taxpayer in writing at least Ten (10) working days before the commencement of a field audit.

የተመሠረተ መስፈርት ተመርጠው ኦዲት የሚደረጉ ታክስ ከፋዮች ኦዲቱ ስለሚጀመርበት የመጀመሪያ ውይይት በአእምሮም ሆነ አስፈላጊ ሰነዶችን በማዘጋጀት እንዲያውቁት አስቀድሞ ይነገራቸዋል።

Taxpayers selected for audit through risk-based criteria shall be informed in advance to prepare both mentally and with relevant documentation for an initial discussion concerning the commencement of the audit.

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የታክስ ኦዲት የሚደረግ መሆኑን ለመግለጽ የሚላክ ማስታወቂያ የሚከተሉትን የሚጨምር ዝርዝር መረጃ ሊኖረው ይገባል፦

ሀ) የሚከናወነውን የታክስ ኦዲት አይነት፤

ለ) ምርመራ የሚደረግበትን የታክስ አይነት፤

ሐ) የኦዲቱ ስራ የሚከናወንበትን ቦታ እና የሚፈጀውን ጊዜ፤

መ) ለኦዲቱ ስራ የሚስፈልጉትን ሰነዶች፤ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች ዝርዝር፤

ሠ) ምርመራ የሚደረግበትን የታክስ ዘመን።

2) The notice to be served in accordance with sub-article 1 of this Article shall include the following details:

a) The type of audit to be conducted.

b) The tax type under consideration.

c) Audit location and expected duration.

d) A list of specific documents, records, or information required for the audit.

e) The tax period(s) to be audited.

19)ከታክስ ከፋዩ ጋር የሚደረግ የመጀመሪያ ስብሰባ እና ስለኦዲቱ ሂደት የሚሰጥ ማብራሪያ

የኦዲቱን ስራ በሚያከናወነው ቡድን እና በታክስ ከፋዩ መካከል በኦዲቱ ሂደት ላይ ውይይት የሚደረግበት የመጀመሪያ ሰብሰባ መዘጋጀት አለበት። በዚህ ስብሰባ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ለታክስ ከፋዩ የኦዲቱን ሂደት እና የሚመረመሩትን የታክስ ከፋዩን ሰነዶች በሚመለከት ማብራሪያ መስጠት እና ከኦዲቱ ጋር በተያያዘ ከተመርማሪው የሚጠበቀውን ማስረዳት አለበት። በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ከታክስ ከፋዩ ወይም ከታክስ ከፋዩ ተወካይ ከታክስ ከፋዮች የታክስ ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።

8. Initial Meeting with the Taxpayer and Clarification of the Audit Process

An initial meeting shall be arranged between the audit team and the taxpayer or taxpayer's representative. During this meeting, the audit team shall provide a clear explanation of the audit process, the time the audit is expected to take, the taxpayer's records to be examined, and expectations for the conduct of the audit. Additionally, the audit team will answer any questions from the taxpayer or the taxpayers representative in relation to the taxpayers liability to taxes.

ክፍል ሦስት
የኦዲት ሥራዎች

SECTION THREE
AUDIT ACTIVITIES

20)የመስክ ኦዲት

9. **Field audit**

1) Following the initial meeting provided under Article 8 of this Directive, the audit

a. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት የመጀመሪያ ውይይት ከተደረገ በኂላ የኦዲት ቡድኑ እንደ አስፈላጊነቱ የመስክ ኦዲት ወይም ምርመራ ለማድረግ መሰማራት አለበት፡፡

b. ይህ የኦዲት ደረጃ ተጨማሪ መረጃ የሚሰበሰብበት፤የሰነዶች ትክክለኛነት የሚረጋገጥበት፤ አግባብነት ላላቸው ሰዎች ቃለመጠይቅ የሚደረግበት እና የኦዲቱን ስራ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡

c. የኦዲት ቡድኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩትን ተግባራት የኦዲቱን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ለማሰባሰብ በሚያስችል ትጋት እና ቅልጥፍና ማከናወን አለበት፡፡

d. የታክሱ ባለስልጣን የመስክ ኦዲት የኦዲቱን ስራ ሽፋን እና ውስብስብነት በሚመጥን አኳኋን እና ሙያውን ባከበረ ሁኔታ በጊዜው መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የመስክ ኦዲቱን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ሆኑ ከተገኘ፤ የታክሱ ባለስልጣን የተሻሻለውን የጊዜ ሰሌዳ ለታክስ ከፋዩ ማስታወቅ አለበት፡፡

team, as necessary, shall proceed with the field audit.

2) This phase of the audit involves the collection of additional data, verification of documents, interviews with relevant persons, and any other activities deemed necessary to complete the audit.

3) The audit team shall carry out the tasks under sub-article 2 of this Article with due diligence and efficiency, ensuring that all relevant information is gathered to support the audit objectives. The audit team will not deviate from the agreed period of the audit except in a case where there is clear indication of errors in other periods prior to those under review.

4) The Tax Authority shall ensure that the field audit phase is conducted in a professional and timely manner, aligned with the scope and complexity of the audit. Should additional time be required to complete the field audit, the Tax Authority shall promptly notify the taxpayer with an updated schedule.

21) የኦዲት ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ ያለበት ግዴታ

የኦዲት ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ፦

a. የታክስ ኦዲተሮች ስራቸውን በቅልጥፍና ማከናወን እንዲችሉ የሚያግዙ ተስማሚ እና ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤

b. የታክስ ኦዲተሮቹ በታክስ አዋጆች መሰረት ተፈላጊ የሆኑትን የሂሳብ መዛግብት፤ የሂሳብ ሰነዶች እና ሌሎች ማስረጃዎችን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ማየት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ በተጠየቀ ጊዜም የእነዚህን ሰነዶች ፎቶኮፒ (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኦርጅናል ሰነዱን ጭምር) መስጠት፤ አለበት፡፡

c. የመስክ ኦዲት በሚካሄድበት ጊዜ ሰነዶች በአብዛኛው ግብር ከፋዩ በሚገኝበት ቦታ ላይ ይመረመራሉ እንጂ እንዲወጡ አይደረግም፡፡

10. Obligations of the taxpayer during audit

During the audit, the taxpayer shall:

1) Ensure that the tax auditors are provided with a suitable and conducive working environment to carry out their duties efficiently.

2) Make available to the tax auditors all books, records, and documents required under the tax Proclamations, and any other relevant documentation andprovide copies of these documents (if necessary including the original documents) as requested.

3) During a field audit, documents are typically consulted and reviewed at the taxpayer's premises without the need to remove them. However, in exceptional cases where the authorised officer cannot use copies and requires the

ሆኖም በተለዩ ሁኔታዎች የተፈቀደለት ባለሥልጣን ቅጂዎችን መጠቀም የማይችልበት እና ለተጨማሪ ምርመራ ዋና ሰነዶችን የሚፈልግ ከሆነ፣ ዋናዎቹ ሰነዶች ሊወሰዱ ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ መደበኛ ሪከርድ የሚዘጋጅ ሲሆን ባለሥልጣኑም ደህንነቱ የተጠበቀ አያያዝ እና ዋናዎቹ ሰነዶች በተስማማበት የጊዜ ገደብ ውስጥ መመለሳቸውን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ይፈርማል።

original documents for further review, such originals may be taken. In such instances, a formal record will be made, and the officer will sign an acknowledgment of receipt, ensuring the safe handling and return of the original documents within an agreed timeframe.

22) አጠቃላይ ኦዲት

1) የታክሱ ባለስልጣን አጠቃላይ ኦዲት የሚያከናውነው፦

ሀ) በስጋት ግምገማ ወቅት ታክስ ከፋዩ በህግ በተደነገገው መሰረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ፤ ገቢውን የማስታወቅ እና ታክስ የመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ ሲታወቅ እና ይህም ሁኔታ የተለያዩ ታክሶችን የሚመለከት ሲሆን፤

ለ) ሌላ አይነት ኦዲት በመደረግ ላይ ባለበት ጊዜ የተገኙ ታክስ ከፋዩ የፈጸማቸው ተገቢ ያልሆኑ አድራጎቶች ኦዲቱ በማይሸፍናቸው በሌሎች ታክሶች ላይ ጭምር ውጤት ያላቸው መሆኑ ሲታወቅ፤

ሐ) ታክስ ከፋዩ ኦዲት እንዲደረግ ሲጠይቅ እና በታክስ ባለስልጣኑ አጠቃላይ ኦዲት አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት፤

መ) አግባብነት ባላቸው በሌሎች የታክስ ህጎች በተገለጹ ሌሎች ምክንያቶች፤

ሠ) ታክስ ከፋዩ በጭብጥ ኦዲት ተደርጎ አከራካሪ ከሆነ እና በቅሬታ ጽ/ቤት በኩል አጠቃላይ ኦዲት እንዲደረግ ትዕዛዝ ሲሰጥ።

2) የታክሱ ባለስልጣን አጠቃላይ ኦዲት በሚያከናውንበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ የሂሳብ ስሌት፤ ግድፈት፤ ገቢን ማሳነስ፤ ተገቢ ያልሆነ የታክስ አሰያየም ወይም በታክስ ማስታወቂያ ወይም ስሌት ረገድ የተፈጸመ ሌላ ማናቸውም ጥፋት ያለመኖሩን ለማረጋገጥ፤ ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን የታክስ አይነቶች በሚመለከት ዝርዝር እና ጥልቀት ያለው ምርመራ ማድረግ አለበት። ይህ የማጣራት ተግባር አግባብነት እስካለው ድረስ የህግ ድንጋጌዎችን ተከትሎ መፈጸም አለበት።

11. Comprehensive Audit

a. The Tax Authority conducts a comprehensive audit:

a) based on a risk assessment, it finds that the taxpayer is not complying with the statutory record-keeping, reporting, and tax payment requirements, and that this behaviour relates to various taxes;

b) the taxpayer has been subject to another type of audit that revealed that the misconduct affects other taxes that are not covered by this audit;

c) The taxpayer requests a comprehensive audit which, in theTtax Authority's opinion, is necessary; or

d) For other reasons under the relevant tax laws.

e) When a taxpayer is subject to an issue audit and is in dispute, and a general audit is ordered by the Complaints Office.

b. When the Tax Authority conducts a comprehensive audit, it conducts a thorough verification of all or part of the taxes to ensure that there has been no case of miscalculation, omission, understatement, misclassification of tax, or any other possible fault that may have occurred in the tax return or calculation. Where applicable, rectification is carried out in accordance with the legal provisions.

23) የዴስክ ኦዲት

1) የዴስክ ኦዲት ኦዲተሩ በቢሯቸው ሆነው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሚያከናውኑት ነው፦

ሀ) በአንድ የተለየ የገቢ ርዕስ ታክስ ከፋዩ ያስታወቀው የሽያጭ ገቢ አጥጋቢ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ ዝቅተኛ ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) የታክስ ማስታወቂያው ከተከፈለው ታክስ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ) አንድ ወይም ከአንድ በላይ የታክስ ደረሰኞች ማስታወቂያ ያልቀረበባቸው ሲሆን፤

መ) የግብር ከፋዩ ወጪዎች ወይም ተቀናሾች የማይፈቀዱ ከሆነ።

ሠ) የታክሱ ባለስልጣን የታክሱን ስሌት ለማከናወን የሚያስችል በቂ ሰነድ ባገኘበት በማናቸውም ሌላ ሁኔታ፤

2) የዴስክ ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ ኦዲት እየተደረገ ስለመሆኑ ታክስ ከፋዩ የጽሁፍ ማስታወቂያ እንዲደርሰው ማድረግ አስፈላጊ አይደለም። ሆኖም ባለስልጣኑ የመጨረሻውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከመላኩ በፊት ታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ወይም በአካል ተገኝቶ ማብራሪያ እንዲሰጥ፣ ጥያቄዎችን እንዲመልስ ወይም ሰነዶችን እንዲያቀርብ መጋበዝ አለበት።

12. Desk audit

a. A desk audit is conducted by an auditor in his or her office on any of the following grounds:

a) If the sales turnover reported on any specific tax head is found to be underreported without adequate justification.

b) If the tax declarations are not corresponding to paid taxes.

c) If one or more invoices were not declared.

d) If the taxpayer expenses or deductions are not allowable.

e) In any other situation where the Tax Authority has sufficient documents that can be used to assess taxes.

b. In the case of the desk audit, it is not necessary to inform the taxpayer in writing that he or she is audited. However, the taxpayer shall be invited to provide explanations, respond to queres or submit documents for any apparent errors before a preliminary assessment notice is issued to him or her.

24) የተመላሽ ኦዲት

a. የተመላሽ ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ የተመላሽ ጥያቄው ትክክለኛ፤ በበቂ ምክንያት የተደገፈ እና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲተሩ ታክስ ከፋዩ ያቀረባቸውን ደጋፊ ማስረጃዎች እና ሰነዶች መመርመር አለበት።

b. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚደረገው ኦዲት ከሌሎች ዓላማዎች መካከል የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ያለመ ይሆናል፤ ተመላሽ የተጠየቀበት የግብዓት ታክስ በሕጋዊ የንግድ ግብይቶች ላይ በአግባቡ መከፈሉን፣ የተገዙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መቀበላቸውን እና ታክስ ለሚከፈልባቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን፤ እንዲሁም አቅራቢው የተመዘገበ እና ጸንቶ የሚገኝ ግብር ከፋይ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

13. Refund Audit

1) When conducting a Refund Audit the auditor shall examine the supporting documentation and records submitted by the taxpayer to ensure that the refund claim is accurate, justified, and in compliance with applicable tax proclamations.

2) The Audit under this Article shall have, among others, the aim to confirm that The input tax claimed has been duly paid on legitimate business transactions, the goods or services purchased have been received and are used for taxable business activities; and he supplier is a registered and active taxpayer.

c. የተመላሽ ኦዲት ሀሰተኛ ደረሰኝ፣ ሀሰተኛ ግብይት ወይም ሀሰተኛ ግዥ ወይም ታክስ ሰብስቦ ከታክስ አስተዳደሩ መሰወር እና የመሳሰሉትን የማጭበርበር ዘዴዎችን የሚያሳዩ ሁኔታዎች ሲኖሩ ሊደረግ ይችላል::

d. የተመላሽ ኦዲት በግብአት ላይ የተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በውጤት ላይ ከተከፈለው ታክስ የበለጠ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ መደረግ አለበት:: ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ የታክሱ ባለስልጣን ታክስ ከፋዩ የተመላሽ ጥያቄ ያቀረበበት ታክስ የተከፈለ መሆኑን እና ታክስ ከፋዩ ተመላሽ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን መመርመር አለበት::

e. በጠቅላላው የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ታክሱ በአግባቡ መመዝገቡ እና ለባለስልጣኑ መከፈሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ቢሆንም፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸው ካልተረጋገጠ በስተቀር የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅራቢው ከአቅርቦቱ ጋር የተያያዘውን የግብዓት ታክስ ለባለስልጣኑ ባለማስታወቁ ወይም ባለማስተላለፉ ብቻ ታክስ ከፋዩ የግብዓት ታክስ ተመላሽ አይከለከልም፤

(ሀ) የግብዓት ታክስ ተመላሹ የሚጠየቅበት ግብይት በአቅራቢው ወይም በአቅርቦት ሰንሰለቱ ውስጥ በተሳተፈ በማንኛውም ሌላ አካል ታክስን በማጭበርበር ከማምለጥ ጋር የተገናኘ መሆኑን ካወቀ ወይም ትክክለኛ እውቀት ከነበረው፤ ወይም፤

(ለ) የግብይቱን ተጨባጭ ሁኔታዎች፣ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቶቹን ባህሪ፣ የአቅራቢውን ማንነት እና ባህሪያት፣ የተከፈለውን ዋጋ እና ከመደበኛ የንግድ ልማዶች አንፃር ያለውን ማንኛውንም ልዩነቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ታክስ ከፋዩ ግብይቱ ከታክስ ማጭበርበር ጋር የተገናኘ መሆኑን ማወቅ የሚገባው ከነበረ::

3) Refund audits may be initiated under various circumstances, including but not limited to when there are indications of irregularities, such as use of false receipts or invoices, false transactions, and patterns consistent with missing trader fraud schemes.

4) Refund Audit may also be carried out when the input Value Added Tax paid exceeds the output tax. In this case, the Tax Authority conducts an audit to determine whether the tax for which the taxpayer is claiming a refund has been paid and that the taxpayer is entitled to the refund.

5) While it is essential to ensure that the tax has been properly accounted for throughout the supply chain, the right to deduct input value added tax shall not be denied solely on the basis that the supplier of the goods or services has failed to account for or remit the output tax related to that supply unless it is proved that the taxpayer;

(a) Knew, or had actual knowledge, that the transaction for which the input value added tax deduction is claimed was connected to fraudulent evasion of tax by the supplier or any other party involved in the chain of supply; or

(b) Should have known that the transaction was connected to fraudulent evasion of tax, taking into account the objective circumstances surrounding the transaction, the nature of the goods or services, the identity and characteristics of the supplier, the price paid, and any deviations from normal commercial practices.

25) **የማሸጋገሪያ ዋጋ ኦዲት**

a. ኦዲተሩ የማሸጋገሪያ ዋጋ ኦዲት በሚያከናውንበት ጊዜ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተከናወነው የእቃዎች፤ የአገልግሎቶች፤ የፋይናንስ እና ግዙፋዊ

14. Transfer Pricing Audit

1) The auditor when conducting a transfer pricing audit shall verify that the pricing of goods, services, financing, intangible

ሃልዎት የሌላቸው ሃብቶች ዋጋ የተወሰነው በማሸጋገሪያ ዋጋ መመሪያ በተተረጎመው መሰረት ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል ስለሚከናወን ግብይት የተቀመጠውን ደረጃ የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

b. የማሸጋገሪያ ዋጋ ኦዲት ግንኙነት ካላቸው እና ግንኙነት ከሌላቸው ሰዎች ተጨማሪ መረጃ መጠየቅን ሊያስከትል የሚችል ሲሆን፤ የታክሱ ባለስልጣን ለወደፊት በማሸጋገሪያ ኦዲት መመሪያ የተመለከተውን ለማሟላት የማሸጋገሪያ ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ ሊያቀርብ የሚገባውን ማስረጃ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

assets etc between related parties as defined in the Transfer Pricing Directive meets the “arm’s length” standard.

2) A transfer pricing audit may require additional information from related and unrelated parties and the Tax Authority may, at a later date, issue a further Directive for compliance with the Transfer Pricing Directive including taxpayer obligations under a Transfer Pricing Audit.

26) የታክስ ማጭበርበር ምርመራ

a. የታክስ ማጭበርበር ምርመራ የሚደረገው የቀረበው ማስታወቂያ፤ ሪፖርት ወይም ሌላ ማናቸውም ድርጊት ታክስ ከፋዩ ሆን ብሎ ከታክስ አዋጆች ተቃራኒ በሆነ የማጭበርበር ተግባር ላይ የተሰማራ መሆኑን የሚጠቁሙ ሲሆን ነው፡፡

b. ስልጣን የተሰጠው ባለሙያ አግባብነት ባላቸው ህጎች ከተደነገገው ጋር ተቃራኒ ባልሆነ ሁኔታ፤ ለታክስ ከፋዩ ማስታወቂያ ሳይሰጥ ስለታክስ ከፋዩ የታክስ መረጃ ለማግኘት በታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ቦታ ወይም ሌላ ማናቸውም ቦታ መግባት ይችላል፡፡ ስልጣን የተሰጠው ባለሙያ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከታክስ ከፋዩ የንግድ ስራ ጋር የተገናኙ ሰነዶችን እና እቃዎችን መፈተሽ እና መያዝ ይችላል፡፡

15. Fraud investigation

1) Fraud investigations may be triggered by irregularities in tax filings, reports, or any other actions that suggest the taxpayer has intentionally engaged in fraudulent activities contrary to the tax proclamations.

2) Without contravening the relevant proclamations, the authorised officer may, without notice, visit or enter business premises of the taxpayer or any other person in search of tax information about the taxpayer. If the authoriser officer considers it necessary, may search and seize objects or documents related to the business activities of the taxpayer.

27) አስተዳደራዊ መቀጫን ስለማስታወቅ

a. የታክስ ህጎችን በመተላለፍ የተፈጸመው ጥፋት ግልጽ እና መቀጫው የሚጣለው በታክስ አዋጆች በተደነገገው መሰረት እስከሆነ ድረስ አስተዳደራዊ መቀጫን ለማስታወቅ የሚሰጠው ማስታወቂያ የታክስ ኦዲት ሳይደረግ ሊሰጥ ይችላል፡፡

b. አስተዳደራዊ መቀጫን ለመጣል የሚሰጠው ማስታወቂያ ገቢን የማስታወቅ ግዴታን ባለመወጣት፤ ገቢን አሳንሶ በማስታወቅ፤ ታክስ ባለመክፈል እና በመሳሰሉት ሌሎች ህግን የመተላለፍ ተግባራት የሚሰጥ ሲሆን፤ አስገዳጅነት ያለው መቀጫን የማስከፈያ ትእዛዝ በመሆን ያገለግላል፡፡

16. Notification of administrative fine

1) Notification of administrative fine may be issued without the necessity of conducting a tax audit where the violation is evident, and the imposition of the fine is in accordance with the legal provisions set forth in the tax proclamations.

2) Notification of administrative fine serves as an enforcement order for the payment of the fine and may be issued for violations such as failure to file returns, underreporting of income, not paying on time or other actions of non-compliance.

ክፍል አራት
የድህረ ኦዲት ሥራዎች

SECTION FOUR
POST-AUDIT ACTIVITIES

28) **ቅድመ- የተሻሻለ ስሌት**

1) ቅድመ- የተሻሻለ ስሌት የሚሰጠው የታክስ ባለስልጣኑ በሚያከናውናቸው መደበኛ የመመርመር ስራዎች፤ በታክስ ኦዲት እና በሌሎች በህግ መሰረት መፈጸሙን የማጣራት ተግባራት የሚደረስባቸውን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ነው።

2) ቅድመ- የተሻሻለ ታክስ ስሌት ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የመጀመሪያ ስሌት ለውጥ ሊደረግበት የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ይፋ የሆነ ማስታወቂያ በመሆኑ፤ የመጨረሻው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ በታሰበው ለውጥ ላይ ምላሽ ወይም ተቃውሞውን ማቅረብ እንዲችል እድል የሚሰጥ ነው።

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚሰጠው ማስታወቂያ እውነትን ወይም ሃሰትን (ተቃርኖን) የማረጋገጥ ሂደት አካል ሲሆን፤በታክስ አዋጆች መሰረት ታክስ ከፋዩ ያለውን አስተያየት ወይም ማብራሪያ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ የሚጠየቅበት ነው።

4) ታክስ ከፋዩ ለስሌቱ መሰረት የሆነውን የተለየ ግኝት በመግለጽ እና ቅሬታውን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በማያያዝ በቅደመ ስሌቱ ላይ ያለውን ቅሬታ፤ ለቅርንጫፉ ምክትል ስራ አስኪያጅ ማቅረብ ይችላል።

5) ለታክስ ከፋዩ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሠጠቱ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጁ በተገኘበት የኦዲት ግኝት ላይ እና የታክስ ከፋዩ ዝርዝር ምላሾች እና ቅሬታዎች ላይ የመውጫ ኮንፈረንስ መደረግ አለበት። በዚህ ኮንፈረንስ ወቅት ኦዲተሮች እና ግብር ከፋዩ ወይም ሕጋዊ ተወካዩ መገኘት ያለባቸው ሲሆን የኮንፈረንሱ ቃለ ጉባኤ በጽሁፍ መያዝ አለበት።

17. Preliminary amended assessment

a. A preliminary amended assessment is conducted based on the findings of the Tax Authority, which may involve discrepancies identified during routine reviews, audits, or other compliance checks.

b. The preliminary amended assessment serves as a formal notice to the taxpayer that the initial assessment is subject to change, providing the taxpayer with an opportunity to respond or contest the proposed changes before the final assessment is issued.

c. The notice to be served as per sub-article 2 of this Article is part of the contradictory process. It is issued in accordance with the legal provisions set forth in the tax proclamations, with clear instructions for the taxpayer to submit any observations or clarifications within a specified time frame.

d. The taxpayer may file a complaint with the Deputy Manager of the branch office, stating the specific findings on which the calculation is based and attaching supporting evidence.

e. Pursuant to Sub-Article 5 of this Article, an exit conference shall be conducted in the presence of the Deputy Branch Manager to review the audit findings, as well as the taxpayer's detailed responses and any objections. The auditors and the taxpayer or their duly appointed representative shall attend this conference, and the proceedings shall be documented in a written record.

29) ከታክስ ማስታወቂያ ውስጥ ስህተቶችን ለይቶ ማውጣት እና ማረም እና ቅድመ- የታክስ ስሌት ማሻሻያ ማውጣት

a. የታክስ ኦዲት ከተጠናቀቀ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 27 እና 28 በተደነገገው መሰረት የታክሱ ባለስልጣን የታክስ ስሌት ስህተት፣ ግድፈት፣ አሳንሶ ማስታወቅ፣ እውነተኛ ያልሆነ መረጃ ወይም በቀረበው ማስታወቂያ ወይም የታክስ ስሌት ላይ ማናቸውንም ሌላ ስህተት ያገኘ እንደሆነ፣ ኦዲተሮች እነዚህን ነገሮች ከግብር ከፋዩ ጋር ኦዲቱን ከመዝጋት በፊት ይወያያሉ:: ይህንን አስከትሎ የታክስ ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ቅድመ-የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ይልካል:: ይህም ማስታወቂያ፦

ሀ) በኦዲቱ ወቅት የተገኘውን ስህተት ወይም ልዩነት የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ፣

ለ) በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ላይ ሊደረግ የታሰበውን ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ፣

ሐ) ተፈጻሚነት ያለውን የታክስ ህግ ወይም መመሪያ አንቀጽ ጨምሮ የማረሚያውን ወይም የማስተካከያውን የህግ መሰረት በሚመለከት ግልጽ የሆነ ማብራሪያ፣

መ) በታክስ ህጎች መሰረት ያለመፈጸም የሚያስከተለውን ቅጣት የሚያሳይ አጭር መግለጫ፣

b. በኦዲቱ ባህሪ ምክንያት አጭር ጊዜ የሚያስፈልግ መሆኑ በታክስ ባለስልጣኑ ካልተወሰነ በስተቀር፣ ታክስ ከፋዩ የኦዲት ግኝቱን በማየት ምላሽ ለመስጠት እንዲችል አጠቃላይ ኦዲትን፣ የማሸጋገሪያ ዋጋ ኦዲትን፣ በጭብጥ ላይ የተመሰረተ ኦዲት እና የተመላሽ ኦዲትን በሚመለክት 5 (አምስት) ቀናት ጊዜ ሊሰጠው ይገባል::

c. ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ የቅደመ- ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያው ተቀባይነት እንዳገኘ ተቆጥሮ፣ የታክሱ ባለስልጣን የመጨረሻውን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ ያዘጋጃል:: ከዚያም ታክስ ከፋዩ በአዋጁ አንቀፅ 54 የተመለከቱትን የአቤቱታ ሂደቶችን መቀጠል ይችላል::

d. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመውጫው ኮንፈረንስ ወቅት ውይይት የተደረገባቸው ጉዳዮች መፍትሔ ካላገኙ ወይም ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ ኦዲቱ የሚመለከተው

18. Identification and rectification of errors in declared taxes and issuance of preliminary amended assessment notice

1) Upon completion of the audit and in accordance with Article 27 and 28 of the Proclamation, if the Tax Authority identifies any miscalculation, omission, understatement, misrepresentation, or any other error in the tax declaration or assessment, the auditors will discuss these items with the taxpayer before closing the physical, at premises element of the audit. The Tax Authority shall then issue a preliminary amended assessment notice to the taxpayer. The notice shall include:

   a) A detailed description of the errors or discrepancies identified during the audit.
   b) Proposed corrections or adjustments to tax return or assessment.
   c) A clear explanation of the legal basis for the rectification, including references to the relevant provisions of the applicable tax laws and regulations.
   d) A summary of any applicable sanctions for non-compliance with tax laws.

2) Unless the tax authority determines that a shorter period is necessary due to the nature of the audit, the taxpayer shall have five (5) working days, to review the findings and respond for comprehensive audits, transfer pricing audits, issue audits and refund audits.

3) If the taxpayer fails to respond within the prescribed period, the preliminary amended assessment shall be deemed accepted and a final notice of amended assessment shall be issued by the Tax Authority. Then, the taxpayer may proceed with the objection processes set out in Article 54 of the Proclamation.

4) Without prejudice to the provisions of Sub-Article 2 of this Article, where matters discussed during the exit conference remain unresolved or require further clarification, the audit division of the Authority may, upon a written request from the taxpayer,

የባለሥልጣኑ የስራ ክፍል ከታክስ ከፋዩ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት በተከታታይ አምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ አጠናቆ እንዲያቀርብ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው በጽሑፍ ሊወስን ይችላል።

authorize an additional period of five (5) consecutive working days to finalize and submit the necessary documentation or response.

30) የቅድመ-ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ ይዘት

የቅደመ - ታክስ ስሌት ማሻሻያ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

a. የታክስ ከፋዩን ስም፤ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድራሻ፡
b. የታክሱን አይነት እና የታክስ ስሌት ማሻሻያው የሚሸፍነውን የታክስ ዘመን፤
c. የታክስ እዳው ስሌት የተከናወነበትን ዘዴ እና ሊከፈል የሚገባውን ታክስ፤
d. የታክስ ስሌት ማሻሻያው ማስታወቂያ ወጪ የተደረገበትን ቀን፤
e. ታክስ ከፋዩ ምላሽ ለመስጠት ያለውን መብት፤

19. Contents of the preliminary amended assessment notice

In addition to the tax elements ,the preliminary amended assessment notice shall include, at a minimum, the following information:

1) The name(s), identification number(s), and address of the taxpayer.
2) The tax type and tax period(s) upon which the assessment notice is based.
3) Calculation of tax liability and amount of tax to be paid.
4) Date of issuance of tax assessment notice.
5) The taxpayer's right to respond or appeal.

31) ለቅድመ-ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ ታክስ ከፋዩ የሚሰጠው ምላሽ

a. ታክስ ከፋዩ አቋሙን የሚያንጸባርቁ ማብራሪያዎችን በመስጠት፤ ማስተካከያዎችን በማድረግ ወይም ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማቅረብ ለቅድመ-ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ ምላሽ የመስጠት መብት አለው። የታክሱ ባለስልጣን የታክስ ከፋዩን አቋም በሚገባ መመርመር እንዲችል ምላሹ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለቅርንጫፉ ምክትል ስራ አስኪያጅ ወይም እርሱ ለሚወክለው ሰው መቅረብ አለበት።

b. የታክስ ኦዲት ቡድኑ የታክስ ከፋዩ ምላሽ እንደደረሰው ምላሹን በመመርመር እንደአግባብነቱ ግኝቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ፤ መቀጫ እና ወለድን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የመጨረሻውን ታክስ ማስላት ይችላል። ይህም የመጨረሻው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ይሆናል።

c. ታክስ ከፋዩ በዚህ መመሪያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ያልሰጠ እንደሆነ፤ የታክሱ ባለስልጣን ማሻሻያው ተቀባይነት እንዳገኘ በመቁጠር፤ ሌላ ተጨማሪ ስነ ሥርዓት ሳያስፈልግ የኦዲት ግኝቱን ሪፖርት ማጠናቀቅ አለበት።

20. Taxpayer's response to the preliminary notice of rectification

1) The taxpayer is entitled to respond to the preliminary amended assessment notice by providing explanations, making corrections, or submitting additional documentation to support their position. The response shall be made to the relevant branch Tax Audit Deputy Manager or delegated officer within the prescribed period under Article 17 of this Directive to allow the Tax Authority to properly assess the taxpayer's position.

2) Upon receiving the taxpayer's response, the audit team shall review and revise the findings as needed, calculate the final tax due, and include any penalties or interest owed. This will form the final amended assessment notice.

3) If the taxpayer fails to respond within the prescribed period, the Tax Authority

may assume acceptance of the proposed adjustments and proceed with finalising the audit findings, without further recourse to the taxpayer.

32) **የመጨረሻውን የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ስለማውጣት**

a. የታክሱ ባለስልጣን የመጨረሻውን የታክስ ስሌት ማሻሻያ የሚያወጣው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፦

ሀ) ታክስ ከፋዩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለቅደመ-ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያው ምላሽ ያልሰጠ እንደሆነ፤

ለ) ለቅደመ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያው ታክስ ከፋዩ የሰጠው ምላሽ ከተመረመረ በኂላ በአዋጁ አንቀጽ 28 በተመለከተው መሰረት የታክሱ ባለስልጣን ታክስ ከፋዩ የሰጠውን ማብራሪያ የተቀበለው ወይም ውድቅ ያደረገው እንደሆነ፤

b. የመጨረሻው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ጨምሮ በአዋጁ አንቀጽ 28(4)፣ (5) እና (6) የተዘረዘሩትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፦\

ሀ) ታክስ ከፋዩ ለቅድመ-ታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ የሰጠው ምላሽ ውድቅ የተደረገበትን ወይም ተቀባይነት ያገኘበትን ምክንያት፤

ለ) የተድረገውን ማስተካከያ፤ መቀጫ እና ወለድን ጨምሮ ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን የመጨረሻ ታክስ፤

ሐ) ታክሱን ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ከፋይ ማንነት፤

መ) የተወሰነውን ታክስ መክፈያውን የመጨረሻ ቀን

21. Issuance of final amended assessment notice

1) The Tax Authority shall issue a final amended assessment notice to the taxpayer under the following conditions:
   a) If the taxpayer fails to respond to the preliminary assessment notice within the prescribed period under article 18 of this directive.
   b) Following the review of the taxpayer's response to the preliminary assessment notice, and in accordance with Article 28 of the Proclamation, the Tax Authority has either accepted or rejected the explanations provided by the taxpayer.

2) The final amended assessment notice shall show the details specified in Article 28 (4, 5 and 6) of the Proclamation, which include the following:
   a) the reasons for accepting or rejecting the taxpayer's explanations in response to the preliminary assessment notice.
   b) the final amount of tax due, including any adjustments, penalties, and interest.
   c) the taxpayer responsible for payment.
   d) deadline to pay the assessed tax

22. **የታክስ ከፋዩ መቃወሚያ**

በመጨረሻው የታክስ ውሳኔ ያልተስማማ ታክስ ከፋይ በአዋጁ አንቀጽ 54 መሰረት ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል።

22. Taxpayer's objection

The taxpayer has the right to file an objection against the final assessment in accordance with Article 54 of the Proclamation.

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

SECTION FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

23. ቅጣት

1) በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ያልፈጸመ ታክስ ከፋይ በአዋጁ የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቅጣት አስፈላጊውን ሰነድ ባለማቅረብ፤ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ

23. Sanctions

1) The applicable sanctions for non-compliance with the provisions of these directives shall be those specified in the Proclamation.
2) The sanction under sub-article 2 of this Article includes penalties for failure to

ምላሽ ባለመስጠት እና በሌሎች ግዴታን ባለመወጣት የሚጣሉ ቅጣቶችን ይጨምራል፡፡

3) የታክሱ ባለስልጣን በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ ቅጣቶችን ፍትሃዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ የማስፈጸም ስልጣን አለው፡፡ ታክስ ከፋዩ የተጣሉበትን ቅጣቶች ሊያውቅ የሚገባ ሲሆን፣ ይግባኝ በሚያቀርብበት ወቅት ቅጣቱን የይግባኙ አንድ አካል አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

24. ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ 2017 ዓ.ም
አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

submit required documentation, failure to respond within prescribed time limits, and other forms of non-compliance.

3) The Tax Authority shall enforce these sanctions in a fair and transparent manner. The taxpayer shall be notified of any penalties imposed, and the taxpayer may contest these sanctions as part of the appeal process.

24. Effective date

This Directive shall enter into force as of the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploading on the official website of the Ministry of Finance.

Addis Ababa 2025

Ahmed Shide

Minister of Finance